# የጎጠኝነት አጥሩ እየተሰበረ የአገር አንድነት የሚያስከብር የተስፋ ጎህ እየቀደደ ነው

አማርኛና ኦሮምኛ ሀብር ፈጥረው የአየር ሞገድ እየሰነጠቁ በጆሮአችን እየተንቆረቆሩ ነው። ፓልቶክ በሚሉት ዘመን አመጣሽ መገናኛ። ...... አብሮነታችን ያስከብረናል ነፃነት ለሁሉም ሲሆን ያኮራል፣ አብረን ስንሆን ያምርብናል የሚሉ አረፍተነገሮች ከየአቅጣጫው ይሰማሉ። ኢትዮጵያ በኦሮሞ ልጆችም የደም ክፍያ አገር ሆና የቆመች የነፃነት ተምሳሌት እንጂ ኦሮሞ እንደ ሕዝብ የማንም ባርያ አልነበረም። ይላል ተናጋሪው አውራ ጣት ይሰቀላል ይሁን ለማለት ..... አበባ ይወረወራል አበጃችሁ ለማለት......

እንደ ሕዝብ የተዋረድንበት፣ ሀገር እንደ ግል ንብረት የተቸረቸረበት፣ በዘር ተነጥሎ የሚታሰርበትና የሚገደልበት ጊዜ ቢኖር ያለንበት የወያኔ ስርዐት ነው። በዘመነ ሚኒሊክ ስለነበረው እያወሳን መርዶ ስንቀመጥ ወያኔ ትኩስ ሬሳ እያስታቀፈን ለቅሶ ይጨምርልናል። ወደፊትማ የቀብር ቦታም ስለማይኖር ባለመሬት ሕንዶች የሬሳ ማቃጠያ የጋዝ ምድጃ ያመጡልንና በሟች ክብደት የማገዶ (የጋዝ) ያስከፍሉናል። ያ ደግሞ ሁለት ሞት ይሆናል። ወያኔን እድሜ ከሰጠነው የበለጠም መዘበቻ እንሆናለን።

እናም ፓልቶክ እንደ አዲስ መንደር አዳዳስ ክፍል እየከፈተ ታዳሚውን በነጻ እያስገባ ነው። ጀነራል ከማል ገልቹንም እየጠበቀ ውይይቱን አሟሙቆታል። ይህንን ክፋት በጋራ ታግለን በክብርና በነፃነት የመኖር መብት የምናስከብርበት ጊዜ አሁን ነው ይላሉ ስደት የታከታቸው የኢትዮጵያ ልጆች። የጥንቱን የጭቆና ታሪክ ተሻግረን አሁን ካለንበት የግፍ አገዛዝ የምንላቀቅበት እንደ ሕዝብ በጋራ እንደ ግለሰብም በተናጠል ልናስብ፣ ልንወያይና ተወያይተንም ወደ ተግባር ልንሸጋገርበት የሚገባን ጊዜ አሁን ነው ሲሉ ተነስ ተነስ ያሰኛል። አለመነሳትም ያስቆጣል!!

እንደ ህብረ ሕዝብ ተከባብረን፣ በነፃነት ለመኖር የሚያግደን አንዳችም ሃይል የለም የሚሉ ሀሳቦች ከግራ ከቀኝ ይነፍሳሉ። ይመስጣል፣ ቀጥሎ ምን ሊሆን ይችላል በሚል ጉጉት ደቂቃዎች እንዳይንቀረፈፉ ያሰኛል። ጣልቃ ጣልቃ የአመለካከት ለውጥ ማድረግ ያልቻሉ ቂምና በቀልን የሚያንቆለጳጵሱ ቆሰቋሽ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን በስድብ መልክ ጣል ጣል የሚያደርጉም አሉ። ልጅን ሲወዱ ከነንፍጡ እንዲሉ እነርሱም አይጠሉም። ስንቱ ጎራዴ የመዘዘ ወደ ሾተሉ መልሶ የለ.... ጊዜ ደጉ.......

በዚህ ስሜት ውስጥ ነበር ጀነራል ከማል ገልቹን ማድመጥ የጀመርኩት። ውብ ነው፣ ውይይቱ በስሜት የሚገፋ (ገን አጥብቆ) ሳይሆን በብልህነት የተሞላ፣ በአርቆ አስተዋይነት የተከሸነ ነበር!! ጂዲ መሌ ጂዲ መሌ ..... ያሰኛል ከአንገት ነቀል ነቀል ከ እግር ዘለል ዘለል እያደረጉ። እንዲህ ነበርን እንዲህም እንሆናለን ...... በልዩነት ደምቀን በአንድነት ተከብረን ኢትዮጵያን ከወያኔ ነጻ እናወጣለን።

ከማል ገልቹ (ማዕረጉን ላለመደጋገም ነው) በኦሮምኛም በአማርኛም ሲናገር ቃላቶች እንደተገራ ፈረስ ይሰግሩለታል። ብልጣ ብልጥ የፖለቲካ ንግግር የለውም። ውስብስብ ትንተናም አይሰጥም የሚታይ የሚጨበጥ እውነት አድርጎ ነው የሚያስቀምጠው። የወታደር ትዕዛዝም እየመሰለ አያስፈራም። የሽምብራ እሸት እየጠረጠሩ የሚሰሙት እንደ ቅርብ ጓደኛ አይነት አወራር ነው። ዳሩ አሁን የካራቴሪ ኤክስፖርት ሩዝ ነው ያለው እኮ እሸት ብረቃችን ሊሆን ነው።

አገር ማለት ሕዝቡ ነው! ስርዐት እንጂ ሕዝብ የሕዝብ ጠላት ሆኖ አያውቅም። አይናችንን እንግለጥ ይላል ጀነራሉ። የጎንደር ገበሬ የወለጋውን ገበሬ የት አውቆ ነው ጠላቱ የሚሆነው? ብሎ ሲተነትን በእርግጥም የስርዐት እንጂ ሕዝብ እንደምን ጠላቱ ይሆናል? ስልጣን የጠማቸው ቁርጥ ያለ አቋም የሌላቸው ኮንትሮባንድ ፖለቲከኞች ወይም ፖለቲካን መተዳደርያቸው ያደረጉ ሰዎችን ጫጫታ መስማት ሱቃቸውን ማስፋፋት ነውና ትኩረታችን ወደ ስራችን ይሁን የሚለው አገላለጥ መንፈስ ያስደስታል።

መነጋገር ማለት መተባበር ማለት አይደለም፣ መተባበርም መጣመር ተብሎ ሊነገር አይገባም። ከግንቦት ሰባት ጋር እጅግ በጣም ጥሩ ግንኙነት አለን ከሌሎችም ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረን መስራታችንን እንቀጥላለን ይለናል የድርጅቱ አመራር።

አገር ከነጉተ ትበልጣለች ተባብረን እናድናት www.ethiomedia.com/aurora/yegott_nikinake.pdf የሚለውን ጥሪዬን ባለፉት አመታት አቅርቤ ነበር ዛሬን አነግ በወሰደው እርምጃ ተደስቻለሁ። እርግጥም ተባብረን እናድናታለን።

የጀነራሉ ምላሽ ዩቲዩብ ላይ በመጫኑ ይህንን አስደሳች ውይይት በራሳችሁ ጆሮ ትሰሙ ዘንድ ይህንን ቁልፍ ተጫኑ
http://www.youtube.com/watch?v=RkOJ5ziLqDY&feature=youtu.be

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com